**“ልጄ ሆይ ቃሌን ብትቀበል ትዕዛዜንም በአንተ ዘንድ ሸሽገህ ብትይዛት ጆሮህ ጥበብን እንዲያደምጥ ታደርጋለህ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ።” ምሳሌ.ምዕ.2ቁ 1-2**

## እራስህን መርምር

ከኃጢአት ነፃ የሆንኩ ታላቅ ነኝ የምትል
አንተ ትንሹ ሰው ትዕቢትህን ከልክል
ክፋትን ጨምረህ እንደገና አትበድል
ከአምላክህ ጋር ታርቀህ በጎን ስራ ቀጥል።
የሚጠብቅ መስሎህ ያለህበት ጊዜ
ጎልቶህ እንዳይሄድ ለሃሳብ ለትካዜ።
ዓይንህ ውስጥ ያለውን ጉድፍ ሳታየው
የሌላውን ለማውጣት እጅ የቀሰርከው
ተመልሰህ የአንተን አንድ ጊዜ አውጣው

አያዋጣምና መፍረድ በሌላው።
ሴራውን ጠንስሰህ በምቀኝነት
ለወንድምህ ጉድጓድ የቆፈርክለት
ፍፁም የወደቅኸው በአመፀኝነት
ጠፍተህ እንዳትቀር ሞት የመጣ ዕለት
እባክህ ተመለስ በንስሃ ሕይወት።
የአምላክህን ውለታ የረሳኸው ለታ
መከራና ስቃይ ይመጣል በተርታ
ቀኑ ሳይመሽብህ ተነስ ተበራታ
ምስጋናና ክብር አቅርብ ለጌታ
አሸበሽብ አጨብጨብ ዘምር በዕልልታ
ሰይጣን ጥሎ ይጠፋል አንዴ ከተረታ
እመን ክርስቶስን ልብህ አያመንታ።
ዋዛ ፈዛዛውን ከምትጫወት
በማታውቀው ነገር ከምትገባበት
አንተ ዝም በልና ሌሎች ይበሉት
ዳር ቆሞ ማስተዋል ይሆናል ትምህርት።
በአንደበትህ አምላክ እንዲከብርበት
በልብህም ነግሶ እንዲኖርበት
ስራህ ብርሀን ይሁን ሁሌ እወቅበት
ከእርሱ ጋራ መኖር ይሰጣል ህይወት
በጎ በረከቱ ያስገኛል ምህረት።
በልብህ የፃፍከው ያማረው ጌጥህ
ጠበቅ አድርገህ ያዘው ሀይል እንዲሆንህ
ለገዛ ትምህርትህ ኑር ተጠንቅቀህ።
እቅድህ እንዲሰምር ምኞትህ እንዲፈፀም
በስራህ ሁሉ ላይ አማኑኤል ይቅደም
በል እንግዲህ በርታ መንፈስህ አይድከም።
አሉባልታን ወሬ አድርገኸው ተስፋ
ሌላው አንተን ሰምቶ በአንተ እንዳይከፋ
አሰናብተውና ከአንተ በኖ ይጥፋ።
ለአንድ ጊዜ አይይደለም በአምላክ መታመን
ታይቶ እንደሚጠፋ ደመና መሆን

ጠንክሮ መስራት ነው የሰማይ ቤትን
በምድር እያለን ጥሪው ሳይደርሰን።
ነፍስህን በብርቱ ስጋ ሲጫናት
ለመቆም አትችልም ከአምላክ ፊት በእውነት
ስጋህን ለመግታት ሁሌ አስብበት።
ስልጣን ስጋ ወስዳ ነፍስ እንዳይከፋት።
የመንፈስን ፍሬዎች ነፍስህ ትወዳለች
እራሷን በመግዛት ትዕግስት አትርፋለች
በሰላም በፍቅር በጣም በልፅጋለች
ቸርነት በጎነት የኄነው ብላለች
እምነት ከየዋህነት አጣምራ ይዛለች
የቤቷን ደስታ ለሌላ አብስራለች።
የስጋ ስራዋን ከእንግዲህ እወቅባት
ዝሙትና ርኩሰት ነግሶባታል ክፋት
ምዋርተኛና አድመኛ ቁጣም በቤቷ ናት
ለመስከር ለመዝፈን ቀዳሚ ስፍራ አላት
ግድያና ድሪያን ሰይጣን አስተምሯት
ጥልና ክርክር አፍርታለች ቅንዓት
ጣዖት አምላኪና መናፍቅ ጭምር ናት
ስጋ ደካማዋን ምክርና አፅናናት
ሁሉንም መርምረህ በግልጽ ንገራት
ከነፍስ ጋር ሆነሽ መንገድ ሂጂ በላት።
በስጋ ሲመችህ ሁሉም ተደላድሎ
አይገባም መራቅ ከአምላክ ኮብልሎ
እንዳይገናኝህ መከራ አድሮ ውሎ።
ዲያብሎስ ክፉ ፍጡር እሳትን አንድዶ
በክፋት በተንኮል ሰዎችን አጥምዶ
አንዱን በአንዱ ላይ እያስነሳ አናድዶ
የኃጢአትን መንገድ ቀስ በቀስ አላምዶ
ልክፍት ሆኖ ቀረቷል ስንቱን አሳብዶ
ስለዚህ ከአምላክ ጋር መኖር ነው ተዋድዶ
የዲያብሎስን ስራ አፍርሶና ንዶ።
የትኛው ነህ አንተ እራስህን መርምር
መጥፎ ከሆነ የያዝከው እንዳይገልህ ይቅር።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
ለንደን (ነሐሴ፡2003 ዓ/ም